በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# የዳ ቪንቺ ኮድ ወይስ? - ክፍል 2

**መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ**


**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com


***ቦታ፡-*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

ጥር ፱ ቀን ፳፻፩ ዓ.ም.

# የዳ ቪንቺ ኮድ ወይስ? - ክፍል 2



# የዳቪንቺ ኮድ ወይስ? - ክፍል 2

## ቅዱስ መጽሐፍ

1.1 የቅዱስ መጽሐፍን ቅዱስነት የማይቀበለው ዳን ብራውን ስለ ቅዱስ መጽሐፍ የራሱን ልብ ወለድ ድርሰት ጽፏል፡፡ ለሥራው ሁሉ አጋዥ የሚሆነውን እውነት በመተው ከእውነት የሚለዮነትን መጻሕፍት ተመርኩዟል፡፡

- «ቅዱስ መጽሐፍንም ለአንባቢው በቀላል መንገድ ለማቅረብ ከመጀመሪያ ጀምረን መመዘን ይኖርብናል» የሚል እሳቤም አለው፡፡
- «ቅዱስ መጽሐፍ ከሰዎች የተገኘ ጽሑፍ ነው እንጂ በፋክስ ከሰማይ አልተላከልንም፤ ከእግዚአብሔርም አይደለም፡፡ በተአምራትም ከደመና አልወረደም፤ በቀላሉ የዘመናት የታሪክ መድበል ነው፡፡ ብዙ ጊዜ ተተርጉሟል፤ ጭማሪ ተደርጎበታል፤ ተሻሽሏል፡፡ በታሪክም የመጽሐፉ ትክክለኛ ቅጂ ተጠብቆ አልቆየንም፡፡» *የዳ ቪንቺ ኮድ ገጽ 231፡፡*
- ቅዱስ መጽሐፍ በእግዚአብሔር መሪነት የተጻፉ ቃላት የሚገኙበት ብቸኛ መጽሐፍ ነው፡፡ ቅዱስ መጽሐፍ በእግዚአብሔር የተገለጸ በመንፈሱም መሪነት በቅዱሳን ሰዎች የተጻፈ ነው፡፡ ለዚህም ደግሞ ብዙ ማስረጃዎች አሉ፡፡
- በመንፈሳዊ ሕይወት ላለ ትምህርት፤ ልብንም ለማቅናት፤ ሰውንም በጽድቅ ለመምራት ያሉ ሥራ ሁሉ መገኛ አምላካችን ነው፡፡ ከርሱ የተገኘውን የቅዱስ መጽሐፍን ትምህርት የተከተሉት ለቅድስና በቅተው ቀዋሚ ተንቀሳቃሽ ቅዱሳት መጻሕፍት ሆነዋል፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ***በ2ኛ ጢሞ 3፡16-17*** ላይ «የእግዚአብሔር ሰው ፍፁምና ለበጐ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል» ብሎአል፡፡
- በአጠቃላይ ቅዱስ መጽሐፍ በእግዚአብሔር የተገለጸ ከስሕተትም ሁሉ በእግዚአብሔር የተጠበቀና በእርሱ ገላጭነት በቅዱሳን ሰዎች የተጻፈ ነው፡፡ ስለዚህ ቅዱስ መጽሐፍ ከእግዚአብሔር ከሰውም የተገኘ ነው፡፡
- ቅዱስ ጴጥሮስ «ቅዱሳን ሰዎች በእግዚአብሔር ተልከው ... በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ጻፉት ...» ብሏል፡፡ ሐዋርያው «በእግዚአብሔር ተልከው» ሲል የእግዚአብሔርን መሪነት፤ «ቅዱሳን ሰዎች ... ተናገሩ» ሲል ደግሞ የሰውን ድርሻ ይናገራል፡፡ ቅዱሳን መጻሕፍትን በተመለከተ ሰዎች በመጻፍ ብቻ ሳይሆን መጻሕፍትንም በመሰብሰብ ተሳትፎ አድርገዋል፡፡ ***2ጴጥ 1፡21 ፤ 2ኛ ጢሞ. 3፡16፡፡***

# የዳቪንቺ ኮድ ወይስ? - ክፍል 2

- ደራሲው በልብ ወለድ ድርሰቱ እንደሚለው ሐዲስ ኪዳን ታሪካዊ መጽሐፍ ሆኖ ሥልጣናቸውን ለማደላደል በፈለጉ ሰዎች ታርሞ የተዘጋጀና የተሰባሰበ አልነበረም፡፡
- ቅዱስ መጽሐፍ መንፈሳዊ ተጽዕኖውን እንደ ጠበቀ ከ850 ወደ ሚበልጡ ቋንቋዎች ተተርጉሟል፡፡ ቅዱስ መጽሐፍ ነቢያት የተነበዩት ትንቢት ሁሉ የተፈጸመበት፤ ትንቢቱም ሆነ ፍጻሜው የሚገኝበት ከእግዚአብሔር የተገኘ መጽሐፍ ነው፡፡ «በነቢይ ከጌታ ዘንድ ... የተባለው ይፈጸም ዘንድ» በሚል መንገድ በትንቢት የተገለጹ ቃላትን ማንበብ በቅዱስ ማቴዎስ ወንጌል ውስጥ በተደጋጋሚ የምናስተውለው ነው፡፡ ***ማቴ. 1:22 ፤2:15 ፤ 4:14 ፤ 8:17 ፤ 12:17 ፤13:25 ፤ 21:4 ፤ 27:35፡፡***
- ቅዱስ መጽሐፍ በተለያየ ጊዜ ፤ በተለያዩ ቅዱሳን ፤ በተለያዩ ቦታዎች የተፃፈ ነው፡፡ እነዚህ የጊዜና የቦታ ልዩነቶች ተጠብቀው ሁሉም መጻሕፍት በአንድነት አንድን ጉዳይ አስረግጠው የሚያስረዱ ወደ ሕይወት መንገድ የሚመሩ መሆናቸው ያለምንም ጥርጥር ቅዱስ መጽሐፍ በእግዚአብሔር መንፈስ መሪነት የተጻፈ መሆኑን ያረጋግጥልናል፡፡
- ቅዱስ መጽሐፍ ለ1500 ዓመታት በላይ ያህል ከ40 በሚበልጡ የተለያየ ባሕል በነበራቸው የእግዚአብሔር ምርጦች ተጽፏል፡፡ ከጸፉትም አንዳንዶቹ እንደ ንጉሥ ዳዊትና ሰሎሞን ያሉት ነገሥታት ነበሩ፡፡ እንደ አሞጽ እረኞች፤ እንደ ዘችርያስ ካህን፤ ከነቢያት ኢሳያስና ሳሙኤል ፤ ሕግን ከሠሩ ሙሴ ፤ ከጦረኞች ኢያሱ ፤ ከዓሣ አጥማጆች ጴጥሮስና ዮሐንስ፤ ከመምህራን ቅዱስ ጳውሎስና ከሕክምና ሰዎች ሉቃስ ጽፈውታል፡፡
- በተጨማሪ ቅዱስ መጽሐፍ የተጻፈው በተለያዮ ቦታዎች ነው፡፡ በሲና በረሀ በይሁዳ ምድረ በዳ፤ በኤድላም ዋሻ፤ በሮም እስር ቤት ፤ በፍጥሞ ደሴት ፤ በጽዮን ቤተ መንግስት ፤ በባቢሎን ወንዞች ዳርቻዎችና በኢየሩሳሌምም ተጽፏል፡፡ በተጠቀሱት ረጅም ዘመናት በተለያየ ጊዜና ቦታ በተለያየ ባሕላዊ ሁኔታ ተጽፎ እስከ አሁን ድረስ በአንድ መጽሐፍ የሚገኘው ከሌላው መጽሐፍ ጋር የሚተባበርበት፤ የነቢያቱ ትንቢት የሐዋርያቱም ስብከት አንድነቱ የተጠበቀበት የመጻሕፍት ስብስብ ከዚህ ዓለም ብናገኝ በእርግጥ ይኸ መጽሐፍ የእግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው፡፡

# የዳ ቪንቺ ኮድ ወይስ? - ክፍል 2

- ቅዱስ መጽሐፍና ቤተ ክርስቲያን አይለያዩም፡፡ ግን ቀደሞ የተገኘው የትኛው ነው? ዶሮ ወይስ እንቁላል? እንዲህ እንደ ማለት ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያን ከቅዱስ መጽሐፍ ትቀድማለች፡፡ በመጀመሪያ የተመሠረተችው ቤተ ክርስቲያን የታተመ ቅዱስ መጽሐፍ አልነበራትም፡፡ ቤተ ክርስቲያንም ቤተ ክርስቲያን ለመሆን የግድ ቅዱስ መጽሐፍ አያስፈልጋትም ነበር፡፡ ይኸ እንዲፈጠር ባንወድም አሁን የሚገኙ ቅዱሳን መጻሕፍት ሁሉ ቢቃጠሉ በቤተ ክርስቲያን ላይ የሚኖራቸው ተጽዕኖ በጣም ጥቂት ነው፡፡ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ነበር ቤተ ክርስቲያን የሮማውያንን የመከራ ዘመን ምዕመናኑን ጠብቃ ያሳለፈችው፡፡ ቤተ ክርስቲያን ባትኖር ቅዱስ መጽሐፍ ብቻውን ለመዳኛችን የሚሆነውን ሊያደርግልን አይችልም፡፡ የት ልንጠመቅ? ልንቆርብ? ቤተ ክርስቲያን «የገሀነም ደጆች አይችላፌትም...» የተባለችውም ለዚሁ ነው፡፡ ***<u>ማቴ. 16፡18</u>***

**1.2** «በተለያዮ የመጽሐፍ ጥቅሎች የተገኙ *ታሪ*ቸዊ ልዮነቶችን ስንመለከት በትክክል ዘመናዊ መጽሐፍ ቅዱስ ፖለቲካዊ አጀንዳ በነበራቸውና ሰው የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን መለኮታዊ አምላክ በማድረግ ይኸንኑ ተጽዕኖ በመጠቀም የራሳቸውን የኃይል መሠረት ለመጣል በፈለጉ ሰዎች የተበረዘ ስብስብ መሆኑን ያረጋግጥልናል፡፡» ***የዳ ቪንቺ ኮድ፤ገጽ 234፡፡***

- *ያለምንም ትክክለኛ ታሪካዊ መረጃ ዳን ብራን «ቅዱስ መጽሐፍ ፖለቲካዊ አጀንዳ ለመሆን በሚያስችል መንገድ የተጠረዘ ነው፡፡» የሚል ክስ ያቀርባል፡፡ ይኸም ክስ ቅዱሳት መጻሕፍት በአንድነት የተሰበሰቡበትን ቀኖናዊ ሂደት ካለመገንዘብ የመነጨ መሆኑን መረዳት አያዳግትም፡፡ አንድን ጽሑፍ በአዲስ ኪዳን እንደ እውነተኛ መጽሐፍ ለመቁጠር ጽሑፋ ሦስት መመዘኛዎችን ማሟላት አለበት፡፡*
- *ፖለቲካና የሰውየው ግላዊ ሁኔታ ግን ከእነዚህ መመዘኛዎች ውስጥ አልተካተቱም፡፡ መመዘኛዎቹ የተዘጋጁት በቀደሙ የእምነት አባቶች አማካኝነት ሲሆን ይህም ማናቸውንም የሐሰት ትምህርቶች በአዲስ ኪዳን መጽሐፍ እንዳይካተቱ አድርጎል፡፡*

# የዳ ቪንቺ ኮድ ወይስ? - ክፍል 2

**መመዘኛዎቹ**

1. **መጽሐፉ ስለ ጌታችንና ስለ ትንሣኤው የዓይን ምስክርነት መስጠት በሚችሉ በጌታችን ደቀመዛሙርት ወይም በሐዋርያት የተጻፈ መሆን አለበት:: የቅዱስ ጳውሎስ ጽሑፎችም ተቀባይነት ያገኙት ራሱ ጌታችን ስለ ተገለጸለትና ከወንድሞቹ ከሐዋርያት ፤ ከቤተ ክርስቲንም ርዕሳን ጋር የሚስማማ ትምህርት በመልዕክቱ ስለ ነበረው ነው::** ***<u>የሐ. ሥራ 8:22 ፤ገላትያ 2:2</u>***
2. **ጽሑፉ ኦርቶዶክሳዊ መሆን አለበት:: ከዕብራውያንና ከሐዋርያት መጻሕፍት ጋርም የሚስማማና ክሕደት የሌለበት መሆን ይገባዋል::**
3. **መጽሐፉ የተጻፈበት ዘመን በነበረች ቤተ ክርስቲያን ተቀባይነት ያገኘ መሆን ይገባዋል:: ተቀባይነቱ የሚመዘነው ራሳቸውን በፈቃዳቸው በለዮ ቡድኖች አማካኝነት አይደለም፤ ይልቁኑ በዚያ ዘመን በነበሩ በቀናች ሃይማኖት በጸኑ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ እንጂ::**

**1.3 «አስቀድሜ የገለጽኋቸው የናግ ሐማዲና የሙት ባህር ጥቅሎት ግልባጮት ቀዳሚ የክርስቲያን መዝገቦች ናቸው:: በሚያስደነግጥ መልኩ ግን አሁን ካሉት ወንጌላት ጋር ምንም መመሳሰል የላቸውም::»** ***የዳ ቪንቺ ኮድ፤ ገጽ 245::***

- **ምእርግጥ የናግ ሐማዲ ግልባጭ በ1945 ዓ.ም. በግብጽ በናግ ሐማዲ አካባቢ ተገኝቷል:: ጥንታዊውም የዚህ መጽሐፍ ግልባጭ የተጻፈው ከ150 ዓ.ም. በኋላ ነው:: የሚበዙት የዚህ መጽሐፍ ክፍሎች የተጻፉት ከ200 - 300 ዓ.ም. ነው:: የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት በጠቅላላ ደግሞ በ100 ዓ.ም.ተጽፈው ተጠናቅቀዋል::**
- **ይኸም ቢያንስ ከጥንቆዊው የናግ ሐማዲ ቅጂ 50 ዓመት አስቀድሞ ማለት ነው:: የናግ ሐማዲ ጽሑፍ የግኖስቲኮች ሐሳብ የተሰበሰበበት የክሕደት መዝገብ ነው:: ጽሑፉ ከተቀበልናቸው የሐዲስ ኪዳንም ሆነ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የተለየ ነው::**
- **የናግ ሐማዲና የሙት ባህር ጥቅሎች ሁለቱም የተለያዩ ሰነዶች ቢሆኑም ዳን ብራውን አንድ አድርጉ አቅርቧቸዋል:: የሙት ባህር ጥቅሎች ከጌታችን መወለድ ረጅም ዘመናት አስቀድመው የተጻፉ ናቸው:: ጥቅሎቹ ቅድመ ክርስትና የተጻፉ ስለሆኑ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ ጨምሮ ማቅረቡ ወይም ማመሳሰሉ ፍጹም ታላቅ ስህተት ነው::**

# የዳ ቪንቺ ኮድ ወይስ? - ክፍል 2

**1.4** «በሐዲስ ኪዳን ከ80 በላይ ወንጌላት ነበሩ:: እስከ አሁን ግን ተቀባይነት ያገኙት የማቴዎስ፤ የማርቆስ፤የሉቃስና የዮሐንስ ወንጌላት ብቻ ናቸው::» *የዳቪንቺ ኮድ፤ ገጽ 231::*

- *አራቱም ወንጌላት በመጀመሪያ መቶ ክፍለ ዘመን ለክርስቲያኖች የተሠራጩና ለአምልኮታቸውም የሚጠቀሙባቸው ነበሩ:: ከዚህ ውጪ ያሉት የናግ ሐማዲ ጽሑፎች እንደ ዳን ብራውን ገለጻ ሰማንያ ሳይሆኑ አምስት ብቻ ናቸው:: አምስቱንም ጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያንም ከላይ ከተገለጹት መመዘኛ ቀኖናት ጋር ስለማይስማሙ አትቀበልም::*

**1.5** «... በራሱ በኢየሱስ እንደ ተጻፈ የሚገመት «Q» ዶክመንት አለ» *የዳንቪንቺ ኮድ፤ገጽ 256*

- *ዳን ብራውን «Q» መዝገብ የሚለው ዘመናዊ መጽሐፍ ነው:: የተጻፈውም በራሳቸው መላ ምት ላይ በተመሠረቱ አንዳንድ ጸሐፊዎች ነው:: የጸሐፊዎቹም እምነት ለማቴዎስ፤ ማርቆስ፤ ሉቃስና ዮሐንስ ወንጌላት የጋራ ምንጭ አላቸው የሚል ነው:: ምንጩም «Q» ሲሆን ከጀርመንኛው «Quelle» ወይም የእንግሊዝኛ ትርጉሙ «Source» ቃል የተወሰደ ሆኖ ትርጉሙም ምንጭ ማለት ነው ይላል::*
- *እንደ ዳ ቪንቺ ኮድ «Q» ድብቅ ምናልባትም በራሱ እጅ የጻፈው የኢየሱስ ክርስቶስ መጽሐፍ ነው:: እውነታው ግን «Q» ከጸሐፊው ምዕናባዊ አቀራረብ ወጭ ምንም አለመሆኑ ነው:: ይህም አንዳንድ ጸሐፊያን የማቴዎስና የሉቃስ ወንጌላት የጌታችንን በርካታ ትምህርቶች ተጋርተው ለምን እንደጻፉ እናስረዳለን የሚል መላ ምት (Hypothesis) ሲሆን ይኸም የዚያ መላ ምት አንዱ ክፍል ነው:: ሐሳቡም ማቴዎስና ሉቃስ ወንጌላቸውን ሲጽፉ አሁን የጠፋ የጋራ ሰነድ ተጠቅመዋል:: ያ የጠፋው ሰነድ የኢየሱስ ክርስቶስን ትምህርቶች አጠቃሎ የሚገልጽ ነበር ይላሉ:: ይህ መረጃ እንዳሉት ቢኖር ያ ሰነድ በቀላሉ የጌታችን የቃሉ ትምህርት ነበር::*

# የዳ ቪንቺ ኮድ ወይስ? - ክፍል 2

1.6 «ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ አዲስ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲጻፍ በገንዘብ ረድቷል:: ስለ ኢየሱስ ክርስቶስም የተጻፉትን እውነታዎች ሰርዞ አምላክ አድርጐ አቅርቦታል:: ስለ እርሱ ያለውን እውነት የሚናገሩ ወንጌላትንም አቃጥሏቸዋል::» *የዳ ቪንቺ ኮድ ፤ ገጽ 233::*

- ከታሪክ እንደምንረዳው ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ቀኖናውያት መጻሕፍትን በተመለከተ ምንም ተሳትፎ አላደረገም:: ራሱ ክርስቲያን ለመሆን የፈለገው በሚልቪያን ድልድይ (Milvian Bridge) በተደረገ ውጊያ ካሸነፈ በኋላ ነው:: ያም ሆኖ ከመሞቱ አስቀድሞ እስከ ነበሩ ጥቂት ሳምንታት ድረስም ለመጠመቅ አልወሰነም ወይም አልፈቀደም ነበር:: በንግሥናውም ዘመን የነበሩ ሳንቲሞችንም ስንመለከት እስከ ዘመኑ ፍጻሜ ድረስ የሮማውያንን የፀሐይ አምላክ ሲያመልክ እንደኖረ ያስረዳል:: ቀኖናውያት መጽሐፍትን የመለየት ሒደት የነበረው ቆስጠንጢኖስ ቄሣር ከመሆኑ በፊት ነው:: ቄሳር የሆነውም በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነበር:: ከመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን አንስቶ በሮም ግዛት የነበሩ ክርስቲያኖች ሁሉ ያለ ልዮነት ተቀብለው የሚጠቀሙባቸው 20 መጻሕፍት ነበሩአቸው::
- እነዚህም:- የማቴዎስ ፤ ማርቆስ ፤ ሉቃስ ፤ ዮሐንስ ፤ የሐዋርያት ሥራ ፤ 13ቱ የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክታት ፤ 1ኛ ጴጥሮስና፤ 2ኛ ዮሐንስ ናቸው:: አከራካሪ የነበሩት የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ዕብራውያን፤ ያዕቆብ ፤ 2ኛ ጴጥሮስ 1ኛ 2ና 3ኛ ዮሐንስ ፤ ይሁዳ እና የዮሐንስ ራእይ ናቸው:: የመጀመሪያው መከራከሪያ እነዚህ መጽሐፍት ከሐዋርያት የተገኙ በመሆናቸውና ባለመሆናቸው ላይ ይነሳ የነበረው የሐሰት ጥያቄ ነው::
- ይኸ ጉዳይ በ140 ዓ.ም. መርቅያን (Marcion) በሚባለው የሥነ መለኮት ምሁር የማቴዎስ፤የማርቆስን፤ የዮሐንስን እና ሦስቱን የቅዱስ ጳውሎስ መልእክታትን ከቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ የመቀነስ ሙከራ ለማድረግ አላስቻለውም፤ ከፍ ያለ ተቃውሞም አምጥቶበት ነበር::
- ቀኖናውያት መጻሕፍትን ለመለየት ሒደት እስከ ቆስጠንጢኖስ ዘመን ድረስ ያልተጀመረ ቢሆን ኖሮ በ140 ዓ.ም. የነበረው የመርቅያን (Marcion) ድርጊት ለክርስቲያኖች ምንም ባልሆነና ባልተቃወሙትም ነበር:: የዚህ ሰው ድርጊት ብዙ የሚከፋፍል ስለነበረ በሮም የነበሩ ክርስቲያኖች በ144 ዓ.ም. ከአንድነታቸው ለይተውታል:: መርቅያን ከተለየ በኋላ የነበሩት የቤተክርስቲያን አባቶች ጠርጡሉስና አርያኖስ ስሕተቱን አስመልክተው ምላሹን ጽፈዋል::


# የዳ ቪንቺ ኮድ ወይስ? - ክፍል 2

- ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ በ330 ዓ.ም. አካባቢ 50 ጥራዝ የክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስ ተባዝቶ (Copy) እንዲቀመጥ በገንዘብ ረድቷል፡፡ ከወንጌላት የመቀነስም ሆነ ወንጌላትን የመቀባባት ሥራ ግን አልነበረውም፡፡ ቆስጠንጢኖስ 50 ቅጂ ከማድረጉ በፊት የነበረውም ሆነ 50 ቅጂዎቹ ክርስቲያኖች ከሚጠቀሙባቸው ከቀደሙት ቅዱሳት መጻሕፍት ምንም የተለየ ቃል እንኳን የላቸውም፡፡
- በ367 ዓ.ም. የእስክንድርያው አባት ቅዱስ አትናቴዎስ ለክርስቲያኖች «የተበከሉና የረከሱ መጻሕፍትን ከእነርሱ ዘንድ እንዲያስወግዱ» እና «በድብቅ የተሠራጩ መጻሕፍትን «እንዳይቀበሉ ጽፎላቸው ነበር፡፡ እንደዚህ ካሉ መልዕክቶቹ የተነሳ አንዳንድ ክርስቲያኖች ቀኖናውያት ያልሆኑ መጻሕፍትን አቃጥለው ሊሆን ይችላል፡፡ እነዚህ የተቃጠሉት መጻሕፍት ክርስቲኖች ከሚቀበሉት ቅዱሳት መጽሐፍት ቀድሞውኑ ያልተካተቱና በኋላ በግኖስቲኮች የተጻፉ ጽሑፎች ናቸው፡፡ «ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች» የሚለው «ሱዳን እጆቿን ...» ብለው ለውጠው እንዳቀረቡበት ያሉትን «መጽሐፍ ቅዱስ» አለመጠቀም ክፉ ስም በእውነተኞቹ ክርስቲያኖች ሊያስጥለው እንደማይችል መገመት የሚያዳግት አይደለም፡፡
- በአብዛኛው የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትን ቀኖናውያት የማድረግ ሥራ የተፈጸመው በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን ነው፡፡ ይኸም ቆስጠንጢኖስ ከመንገሡ ከሁለት ምዕተ ዓመታት አስቀድሞ ነው፡፡ ሐዲስ ኪዳን በንጉሥ ቆስጠንጢኖስ አማካኝነት ኢየሱስ ክርስቶስን አምላክ ለማድረግ አጊጦ የቀረበ አይደለም፡፡
- ቆስጠንጢኖስ በሮም ቄሣር ሆኖ የተሾመው ክርስቲያኖች ጌታችንን መለኮታዊ አምላክ እንደ ሆነ ካመኑ በኋላ በ306 ዓ.ም. ነበር፡፡ በዳ ቪንቺ ኮድ መጽሐፍ በገጽ 233 የተቀመጠው «ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ተብሎ የተወሰነው በቆስጠንጢኖስ ወይም በጳጳሳቱ ነው» የሚለው መግለጫም ፍጹም ልብ ወለድ ነው፡፡

# የዳ ቪንቺ ኮድ ወይስ? - ክፍል 2

- የክርስቲያኖችን መጻሕፍት ሥልጣን የሚክዱ ጸሐፍት እንኳን ከጌታችን ሞት ትንሣኤና ዕርገት በኋላ በተከታዮቹ 20 ዓመታት ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ክርስቲያኖች ሕይወት በሮም ግዛት ሁሉ ለምትገኘው ቤተ ክርስቲን የጻፈውን መልዕክት ይቀበላሉ:: በ40 ቹና 50ዎቹ ቅዱስ ጳውሎስ በጻፈው መልዕክቱ ጌታችንን «የእግዚአብሔር ልጅ፣ ሁሉ በርሱ ሆነ፣ ከሁሉ በላይ የሆነ እግዚአብሔር የተባረከ ይሁን» በማለት ጽፏል፡፡ በኋላም ለፍልጵስዩስና ለቆላስይስ ሰዎች በጻፈው መልዕክቱ ጌታችንን "እግዚአብሔር ነው ፤ በእግዚአብሔርነቱ ሲኖር ሳለ ፤ የማይታየው እግዚአብሔር ምሳሌ... " ብሎ ጽፏል:: እነዚህ ጽሑፎች ተቀባይነት አግኝተው በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን ተደንቀዋል:: በዚህም ዘመን በነበሩ ክርስቲኖችም ተባዝተው ተሠራጭተዋል::
- በ100 ዓ.ም. በግብጽ የተገኘው የቅዱስ ዮሐንስ ወንጌል ቁራጭ ጌታችንን «ጌታዬና አምላኬ» ይለዋል:: ከዮሐንስ ወንጌልም በፊት የተሰራጩት ወንጌላት ጌታችን እግዚአብሔር እንደ ሆነ የሚመሰክሩ ናቸው::የክርስቲያን ጠላቶች የነበሩ ቀደምት መናፍቃን ራሳቸው ክርስቲኖች ጌታችንን መለኮታዊ አምላክ ብለው እንደሚያመልኩት ያውቁ ነበር:: ***<u>ሮሜ 9:5 ፤ 1ኛ ቆሮ 8:6 ፤ 2ኛ ቆሮ 4:5፤ ገላ 1:1-3 ፤ ገላ 2:20 ፤ 2ኛ ተሰ 2:16 ፤ ፊሊ 2:6 ፤ ቆላ 1:15-16 ፤ ዮሐ 1:1 ፤ ዮሐ 20:28 ፤ ማቴ 1:23 ፤ ማር 1:1 ፤ ሉቃስ 1:35::</u>***
- በተረፈ ግን ወንጌላት የሚገልጹት የጌታችንን የባህርይ አምላክነት ብቻ ሳይሆን በፍጹም ተዋሕዶ ፍጹም አምላክ መሆኑን ነው:: ***<u>1ኛ ዮሐ 4፤2::</u>***
- አምላክ ሰው ሆኖ ሰውን የማዳኑ ምስጢር በቅዱስ መጽሐፍ ካልተገለጸ ቅዱስ መጽሐፍ መጻፉ ፈጽሞ ባላስፈለገ ነበር:: ዳን ብራውን እና ተከቶዮቹ ስለ ጌታችን ሰው የመሆን ምስጢርም ሆነ ስለ ባሕርይ አምላክነቱ ለመረዳት ሐዲስ ኪዳንን በጥንቃቄ ማንበብና ምስጢሩንም ከሚያስረዷቸው የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት መረዳት ይኖርባቸውል:: ለሚደመረውና ለሚቀነሰው የሂሳብ ትምህርት እንኳን ጥሩ መምህር ፍለጋ ወላጆች እንደሚደክሙ ተማሪዎችም ዕውቀትን ለመጨበጥ እንደሚጣጣሩ ይታወቃል:: ታዲያ መጽሐፍ ቅዱስንም በዕውር ድንብር ከሚራመዱበት ቢማሩትና ቢያጠኑት ከሥጋዊ ብቻ ሳይሆን ከመንፈሳዊ ቁም ነገር ያደርሳቸዋል::

# የዳቪንቺ ኮድ ወይስ...?




አዘጋጅ፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

ነሐሴ 1998 ዓ.ም.

# ይቆየን።

For your queries or questions E-mail:
kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org